ባየሁት ወይስ በሰማሁት ነገር ልምከርህ ...

አል-መንሱር በኸሊፋነት በተሾመ ጊዜ ሙታሊል ኢብኑ ሱለይማን እርሱ ዘንድ ገባ። አልመንሱርም "ሙታሊል ሆይ ምከረኝ።" አለው።

ሙታሊልም " የምእመናን መሪ ሆይ ባየሁት ወይስ በሰማሁት ነገር ልምከርህ።" አለው። "ባየኸው ነገር ምከረኝ።" አለው።

"አሚራችን ሆይ! ኸሊፋው ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ አሥራ አንድ ልጆች ነበሩት። ሲሞት ደግሞ አሥራ ስምንት ዲናሮችን ብቻ ነበር ትቶ ያለፈው። በአምስቱ ዲናር ከፈን ተገዛለት። በአራቱ ደግሞ የመቃብር ቦታው ተገዛ። ቀሪው ዲናር ለልጆቹ ተከፋፈለ። ሂሻም ኢብኑ ዐብዱልመሊክም አሥራ አንድ ልጆች ነበሩት። ሀብቱ የበዛ ነበር። ዉርሱን ሲከፋፈሉ አንዳንድ የወርቅ ጉማጆች በመጥረቢያ ጭምር እየተከፈለ ነበር ለልጆቹ የተሠጣቸው። አሚራችን ሆይ! በአላህ እምላለሁ! ከዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ ልጆች መካከል አንዱ የሆነ ቀን በአላህ መንገድ ላይ ለሚደረገው ትግል መቶ ፈረሶችን ሲመፀዉት አይቻለሁ። ከሂሻም ልጆች መካከል ደግሞ ለማኝ የሆነ አጋጥሞኛል። "

ዑመር ኢብኑ ዐብዱልዐዚዝ አምስተኛው የሙስሊሞች ኸሊፋ በመባል የሚታወቁ ቅን እና ፍትሃዊ መሪ ነበሩ። ልጆቻቸዉም በመልካምነታቸው የሚታወቁ ናቸው። አንድ ወላጅ ለልጁ ከሚያወርሣቸው ነገሮች ሁሉ ትልቁ ዲን ነዉና ለልጆቻቸው ከሀብት ይልቅ ዲንን አወረሱ። ደግ አባቱ ከዚህች ዓለም ጥቅም ለልጆቹ ምንም ሳይተው ቢያልፍ እንኳ አያሳስበዉም። የአላህን ፍራቻ ከተወላቸው በቂ ነው። በርሱ ሁሉን ነገር ይማራሉ፤ ከመጥፎ ነገር ሁሉ ይጠበቃሉ።

ገንዘብ ስለበዛ አይደለም ሰዉን የሚጠቅመው። ዋናው በረካው ነው። ከዲን ይልቅ ዱንያዊ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ልጆቻቸዉን የጠቀሙ መስሏቸው ገንዘብ፣ ሀብትና ንብረት በማውረስ የጎዱ ብዙ ናቸው። ምንም እንኳን ቤተሰብን ለድህነት ጥሎ ዱንያን መሻገር መልካም ባይሆንም ገንዘብ በጥሩ ሰው እጅ ካልሆነ እንደሚያጠፋና ኻቲማን እንደሚያበላሽ መታወቅ አለበት። ከላይ ያየናቸው መሪዎች በሙስሊሞች ላይ የተሾሙ ቢሆንም ከሀብት አንፃር የተከተሉት መንገድ የተለያየ ነበር። በዚህም ሁለቱም የዘሩትን ፍሬ አግኝተዋል። **አገኘን ብላችሁ አታግበስብሱ። ሐላሉ ላይ አተኩሩ። አላህ ሐላል ነገር ላይ በረከቱን ይጨምራል።**

የማይሞሉ ክፍተቶች ...

ምርጧ ፋጢማ (ረ.ዐ.) የነቢያችን የአላህ መልዕክተኛ የነቢዩ ሙሐመድ ሶ.ዐ.ወ. ቆንጆዋ ልጅ፤ በመልከም፣ በፀባይም በአካሄድም ጭምር ቁርጥ አባቷን ትመስል ነበር ይባላል። ትህትናዋና ደግነቷ በዝቶ ይወራላታል። ለአጎታቸው ልጅ ለደጉ ዐሊ ረ.ዐ. በእጃቸው የዳሯት ተወዳጇ ፋጤ ከርሣቸው ወደ አኺራ መሸጋገር በኋላ ምድር ላይ የቆየችው ለስድስት ወራት ብቻ ነበር። ከርሣቸው ልጆች መካከልም ወደኋላ የቀረችው እሷ ብቻ ነበረች።

ነቢዩ ሶ.ዐ.ወ. ልጃቸው ፋጢማን አብዝተው ይወዷታል፤ እንደ አባት ቅርባቸው፣ እንደ ልጅ ሚስጢረኛቸው ነበረች። በልዩ ሁኔታ ያዩዋታል፣ ስትመጣ ተነስተው ሁሉ ይቀበሏታል፣ ከጎናቸው አስቀምጠው ያወጓታል፤ እርሷም እጅግ እጅግ ትወዳቸው ነበር። ሊሞቱ አካባቢ ጭምር በቅርቡ ወደኛ ትመጪያለሽ ብለው በጆሮዋ ሹክ ብለዉላታል። እርሷም ሳቀችም አለቀሰችም። ሳቋ ወደርሣቸው በቅርቡ የምትሄድ በመሆኗ መደሠቷን፤ እንባዋ ደግሞ እርሣቸው ተለይተዋት ሊሄዱ በመሆናቸው ማዘኗ ነበር። በበኩሌ ፋጢማ እነዚያን ከርሣቸው ተለይታ የቆየችባቸዉን ወራት እንዴት አሳልፋ ይሆን የሚለዉን ነገር ሳስብ ጭንቅ ይለኛል። ኢማም ዘሀቢ ሁኔታ "ፋጢማ ከርሣቸው መለየት በኋላ በቁሟ እየሚሟች አለቀች።" በማለት ይገልፁታል።

"ሟሟች" የሚለዉን ቃል አዩልኝማ። አዎ አንዳንድ ሐዘን በቁም ያሟሟል። በሕይወት ይጨርሳል። በሀሳብ ይገድላል። አንዳንድ ሰው ዱንያን ለቆ ከጎናችን ተነጥሎ ሲሄድ ብቻዉን የሚሄድ አይምሠላችሁ። ሩሓችን ይዞ የሚሄድ አለ፤ ቀልባችንን ይዞ የሚሄድ አለ፤ ጉልበታችንን፣ ተስፋችንን፣ ብርሃናችንን፣ ደስታችንን ይዞ የሚሄድ አለ። የአንዳንድን ሰው ሐዘን በመፅናናት አይሻገሩትም። እያደር ይቆረቁራል።

ወዳጆቼ! የአንዳንድ ሰዉን ቦታ ማንም ምንም አይሞላዉም። ነቢዩ የዕቁብ አሥራ አንድ ልጆች ነበሯቸው፤ ግና ስለ ልጃቸው ዩሱፍ እንዳዘኑ እንደተከዙ ዐይናቸው ጠፍቷል። ነቢያችን ሙሐመድም ሶ.ዐ.ወ. አሥራ አንድ ሚስቶች ነበሯቸው። ግና ሰው ሁሉ እስኪገረምባቸው ድረስ ኸዲጃን እያወሱ ስለ ኸዲጃ እንዳወሩ ምድርን ተሻግረው አኺራ ዘልቀዋል።

ሰው ባይሞትብን እንኳ ዱንያ በየቀኑ ለቅሶ ናት። የሁላችሁን ለቅሶ መድረስ ብችል እንዴት ደስ ባለኝ። አብሸሩልኝም። ሶባሐል ኸይር ወዳጆቼ!

ብልህነት

✓ ከአባትህ ምከሩን ቁጭ ብለህ ስማና የዱንያን ምንነት እወቅበት፤

✓ ከእናትህ ዱዓዋን ተንበርከከህ ተቀበልና ቀንህን አሳምርበት፤ መከራህን ገፍተርበት፤

✓ ከጊዜህ ጥቂት ወስደህ አንዲት ሱጁድ ዉረድና ሰላደረገልህ ነገር ሁሉ አምላክህን አመስግንበት።

ምጽዋት

✓ የመፀወተ፤ አላህን የፈራ፤ በአስልምናም ሆነ በመጨረሻው ቀንም ያመነ አላህ ነገሮችን ያገራለታል።

✓ የነፈገ፤ የኮራ፤ በአስልምናም ትንሳኤው ቀንም ያስተባበለ አላህ ነገሮችን ያከብድበታል። ያቸጋግረዋል።

✓ የዚህን ሀሳብ የያዘ አንቀጽ ቅዱስ ቁርአን ላይ አለላችሁ። (አል-ለይል ፡ 4-10)

✓ ጉዳይ ሲጠናባችሁ፤ ስትታመሙ፤ ስትቸገሩ፤ መከራ ሲያገኛችሁ መፍትሄው መመጽወት ነው። ሶደቃ ነው። ባይኖራችሁም ካላችሁ ነገር ማካፈል ነው።

ፈዋሽ መድኃኒቶች ...

በደንብ መተኛት፤ በጠዋት መነሳት፤ የእናት አባትን ሓጃ መፈፀም፤ ለቤተሰብ በጎ መዋል፤ ጓደኛን ማስታወስ፤ ለራስም ሆነ ለሌላው ዱዓእ ማድረግ፤ ከጥሩ ሰዎች ጋር መዋል፤ አላህን ከሚያስታዉሱ ጋር ማውራት፤ መጥፎ ጓደኛን መራቅ፤ ሰዉን መውደድ፤ ቅንነትን መላበስ፤ የተቸገረን መርዳት፤ በሥራ ቢዚ መሆን፤ ...

ጥሩ ቁርስ መብላት፤ ጥሩ መጽሐፍ ማንበብ፤ ጊዜን በአግባቡ መጠቀም፤ ሻወር መውሰድ፤ ጥሩጥሩዉን ማሰብ፤ መሳቅ መጫወት፤ ፈገግታን ማደል፤ ራስን ማዝናናት፤ ራስን መንከባከብ፤ ለራስ ጊዜ መስጠት፤ አዳዲስ ሰዎችን መተዋወቅ፤

ሶላትን መስገድ፤ ቁርአን ማንበብ፤ ዚክር ማብዛት፤ ኢስቲግፋርን ማዘውተር፤ መስጂድ ዉስጥ ጥቂት መቆየት፤ ሁሌም አላህን ማሰብ፤

መጥፎ ስሜቶችን ማባረር፤ ሀሳብ ጭንቀትን ለማስወገድ፤... እንዲህ እንዲህ ካልሆነ ዱንያን በቀላሉ አንሻገራትም። እያታለልናት፤ እያባበልናት ካልኖርን ዱንያ በአለንጋዋ አትምረንም ወዳጆቼ።

ለኸይር ነው ወዳጄ..

አትዘን:: "ሌላው ቀርቶ ኃጢአት ጭምር መልካም ነገር ሊይጠፋዉም::" ይላሉ ታላቁ ሸይኽ ኢማም ኢብኑ ተይሚያ:: ለምን አትልም ወይ:: እንዴት ብለህ ጢይቀኝማ:: ምንም እንኳን ኃጢአት የተጠላ ነገር ቢሆንም በተሊይ ሳታስበው ድንጉት ከወደቅከና ከሠራኸው በኋላ ደስታ ይርቅሃል:: ታለቅሳለህ፣ ትሰበራለህ፣ በራስህ ታዝናለህ፣ ራስህን ትንቃለህ፣ ራስህን ትወቅሳለህ፣ ሰላም ታጣለህ፣ ሕይወት ያስጠላሃል፣ እንቅልፍ ይርቅሃል:: ይህ መሰበር፣ ማልቀስ፣ ሙተከዝ፣ ራስን መውቀስ እና በራስ ማዘን ... በራሱ ኸይር ነገር አለው:: ትልቅ ምት ነው፤ ማንቂያ ደወል ነው፤ እንድትፀፀት ያድርግሃል፤ ወደ አላህ እንድትመለስ ያነሳሳሃል፣ ችግርህን እንድታምን፣ ድከመትህ እንድትቀበልና እንድታስተካከለው ይጋብዝሃል::

ወዳጆቼ! መጥፎ ነገር ባይኖር ኖሮ የመልካም ነገር ዋጋው ሊይገባንም ነበር:: ቆሻሻ ባይኖር የንፁህ ነገር ምንነትን እንረዳም:: ተቃራኒ ነገሮች ባይኖሩ ኖሮ በነገሮች መካከል ያለዉ ልዩነት ሊይታየንም ነበር:: ኃጢአት ባይኖር ኖሮ የጽድቅን ነገር ዉበት እንረዳም::ለመታረም ያግዛል:: ኃጢአት ምን ያህል አስቀያሚ ነገር እንደሆነ ያወቅነው ድንገት ወድቀንበት ስላየን ነው:: ይህ መሆኑ በአንድ በኩል ኸይር ነው:: ኃጢአት እሣት እና አስቀያሚ ነገር መሆኑን አውቀን የበለጠ እንድንጠነቀቀው፣ እንድንርቀው፣ እንድንጠየፈው ያደርገናል:: አላህ መመለሱን ይስጠን እንጂ መውደቃችን ለበጎ ነው እንበል:: በብዙ መልኩ አንቅቶናልና ኃጢአት በርግጥም ጠቅሞናል::

ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ መውደቃችን ለኸይር ነበር ማለት ነው:: እንማርበታለን፣ እናተርፍበታለን፣ እንለወጥበታለን:: ወደተሻለ ነገርና ሥራ መንደርደርያ ይሆነናል:: የለወጠን ነገር ነፍስ ዘራብን እንጂ አልገደለንም:: በርግጥ ኃጢአት መልካም የሚሆነው ስንፀፀት ነው:: ስንቶብት ነው:: ስንሻሻልበት ነው:: በቁርጠኝነት ወደ አላህ ስንመለስ ነው:: ያልተሻሻሉበት ዉድቀት፣ ያልተማሩበት ስህተት፣ ራስን ያላዩበት ድልጠት ፈጽሞ ኸይር ሊሆን አይችልም::

ወዳጆቼ! የፈሰሰ ዉሃ አይታፈስምና ኃጢአት ላይ ከወደቃችሁ በኋላ እዚያው ሙሉ ዕድሜያችሁን ስታለቅሱ አትከረሙ:: ቶብቱ:: ዉድቀታችሁንም ለመነሳታችሁ መሰረንጠርያ አድርጉት::

ሶባሐል ኸይር!!

ጀነትን አስቡ

ዱንያ ላይ ከማንም በላይ ተንገላትቻለሁ፣ ከሁሉ በላይ ጉዳት ደርሶብኛል ... ብዬ ባላስብም እንኳ ዱንያ ጢባጥቢ ተጫውታበት ካሳደገቻቸው መካከል አንዱ ነኝ አምናለሁ። መከራን በያይነቱ አይቻለሁ። በችግር አርጩሜዋ ተገርፌ፣ ከዱንያ የእንግልት ጡጦ ቢደንብ ጠብቼ እንዳይሆኑ ሆኜ ያደግኩ ሰው ነኝ። በዚሁ ድባብ ዉስጥም ከልጅነት እስከ አዋቂነት ዕድሜ ዘልቄያለሁ። ከደረስነት ሕይወት እስከ ስደት ዓለም ብዙ ቀምሻለሁ። ዛሬ ላይ የራስ ቅሌን ከዳር እስከዳር፣ ፊቴንም ከአገጭ እስኪጆሮ የወረረው ነጭ ሽበት የዕድሜ ነው ብላችሁ እንዳታስቡ። የመጣሁበት የእንግልት መንገድ ያፈላው ምርት ነው። አልሐምዱ ሊላህ። ምናልባት አሁን ላይ እየቆምኩ ይሆናል። ቢሆንም ግን ዱንያ ላይ አፈር ልሰው ከተነሱ ሰዎች መካከል አንዱ እኔ ነኝና ዱንያ ያደረገችኝን አልረሳም። አለመርሳቴ ዱንያን አውቄያት እንድጋፈጣት ያግዘኛል። አሁን ዱንያን ተጋፍጬ ምን እያደረግኳት እንደሆነ እኔ ራሴ አውቃለሁ።

አናም ወዲጆቼ ... እንኳንም ተገረፍኩ፣ እንኳንም ተቸገርኩ፣ እንኳንም ተጠማሁ፣ እንኳንም ተራብኩ፣ እንኳንም ተሰደድኩ። በዚህ ሁሉ መሀል ዱንያ በደንብ አስተምራኛለች፣ በሚገባ ቀርፃኛለች፣ ቆንጆ ልምድ ሠጥታኛለች፣ ጥሩ አድርጋ ሠርታኛለች፣ ቀጭን ብሆንም ፈሪ አድርጋኛለች።

በዱንያ የችግር ቀናቶች መካከል የዱንያ ባህሪዋ ገብቶኛል፣ ምንነቷን ተረድቻለሁ፣ ማንነቷን አውቄያለሁ። አንድን ነገር ያወቀ ሰው ደግሞ በዚያ ነገር ብዙ አይገረምም። አሁን ላይ ዱንያን አልፈራትም፣ ችግር መከራዋ አያሸብረኝም፣ ፈተናዋ መዓት መስሎ አይታየኝም። የኖረበት ይደነድናልና ብርቱ ሆኜያለሁ። እንዲህ ስል ግን የዱንያን ፈተና በራሴ ላይ አጠራለሁ ማለቴ አይደለም። ጌታዬ ሆይ ወደፈተና አታስገባን። ተቸግሬ አይቻለሁና በሰዎች ፈተና ብዙ አይገርመኝም። ሰዎች ስለ ችግር፣ ስለ ፈተና ሲያወሩኝ አብሽሩ ያልፋል ማለት የማበሳጨም ለዚሁ ነው። በርግጥ ስንትና ስንት አያልፍም ብዬ ያሰብኩት ነገር ሁሉ በሕይወቴ ዉስጥ አልፏል መሠላችሁ። አይ ዱንያ።

ይህ መጽሐፍ ባንድ በኩል ልምድ ማካፈያ መድረኬ ነው ብዬ አስባለሁ። አናም ዱንያ ላይ ስኖር ፈተናዋን ተቋቁሜ እንድኖር፣ በአድካሚው ሥራዬ ላይ እንድፀና እንደ ብርታት መርፌ ከምጠቀምባቸው ነገሮች መካከል አንዱን ልጠቁማችሁ - ጀነትን ማሰብ ነው።

እምነ ወላጆች፣ ምን መሠላችሁ ... ለመኖር ስል፣ ሰው ለመሆን ስል፣ በሕይወት ለመላቀጥ ስል፣ ለመሳቅም ስል፣ ወደፊት ለመወርወር ስል ... ብዙ ነገሮችን በጀነት አላተርፋለሁ። ጌታዬ አላህ ጀነት ያስገባኝ አያስገባኝ የማላውቅ ብሆንም ግና በርካታ ጉዳዮቼን ከጀነት ጋር አስተሳስሬአለሁ። ለምሳሌ በጠራራው ፀሐይ ከባድ ዕቃ ተሸክሜ ስሄድ ከደከመኝ አረፍ ብዬ ኢንሻአላህ እልፍል አየልኩ ጀነትን አስባለሁ። ታክሲ ለመጠበቅ ረጅም ሰዓት እሻፌ አስከነጭነጭኩ ድረስ ቆሜ ከደከመኝ በጀነት አርፋለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ስለ ዱንያ ላይ ድካሜ፣ ሀመሜ፣ ጠጣጠረዬ፣ እንግልቴ፣ ሁሉ አስብ አስብና እንዴት ልርሳው ስል ጀነትን ፈትለፈቴ አመጣለሁ። ጌታዬ ሁኔታዬን ሁሉ ታያለህ ድካሜን፣ ላቤን፣ መከራት መጥቆሬን፣ መገርጣቴን ሁሉ በጀነት ካሰኝ ብዬ አለምናለሁ፤ ጌታዬን እማፀናለሁ።

እም ጀነትን አልማለሁ ... ጉልበት ለማግኘት፣ ለመበርታት፣ ለመጠንከር ስል በድካሜ ላይ በሀላብ ጀነትን እጎነጫለሁ፣ በቁስሌ ላይ ጀነትን አፈሳለሁ። ያኔ እበረታለሁ። በመከራዬና ፈተናዬ ጢስ ሁሉ ጀነት ለኔ ቅርብ ናት። ሰው ቢበድለኝ፣ ያላግባብ ቢዘልፈኝ፣ ከብሬን ቢያዋርድ፣ አሳንሶ ቢመለከተኝ፣ ቢንቀኝ፣ ሥሜን ቢያጠፋ፣ ቢሰርቀኝ፣ ቢገፋኝ ... አይዞኝ ሙሐመዱ በጀነት ትካሳለህ ብዬ እኔን አጽናናለሁ፤ ራሴን አበረታ ታዋለሁ።

ጀነትማ በምናብ ዮቶግር ጊዜ ደራሼ ናት። በድካም ወቅት ተስፋዬ ናት። ጀነት በበሽታዬ መድኃኒቴ፤ ጀነት በዝለቴ ኪኒኒዬ ናት። ጀነትን ሳስብ ድካሜ ሁሉ ብን ብሎ ያጠፋል፤ ጀነትን ተስፋ ሳደርግ ችግሬን ሁሉ እረሳለሁ። ሕመሜን በሙሉ አዘነጋለሁ። መታገስ በማልችለው ነገር ላይ ጭምር ጥርሴን ነክሼ አታገሣለሁ። ወዳጆቼ! ጀነትን ማሰብ ዱንያ ላይ ለሚገጥሙን በርካታ ፈተናዎች መድኃኒት ነው። ለብዙ አካላዊም ሆነ መንፈሳዊ ህመሞች ፈውስ ነው። ለብዙ ቁስሎችም ሕክምና ነው። የአላህ መልዕክተኛ ሶ.ዐ.ወ. ባመካ ሰዎች ከባድ ማሰቃየት ለደረሰባቸው ለያሲር ቤተሰብ ምንም ሊያደርጉላቸው ባለመቻላቸው በጀነት ነበር ያጽናኗቸው "የያሲር ቤተሰብ ሆይ ታገሱ፤ ቀጠሮአችሁ ጀነት ነው።" ነበር ያሏቸው። እነ ቢላል ጀነትን እያሰቡ በኡመያ የግርፋት ቅጣት ላይ ታግሰዋል። ሰሚራ የተባለች ጥቁር ሴት ጀነትን አስባ ከሚጥላት በሽታ አለመዳንን መርጣለች። ጀነትን ያሰቡ ደጋግ ሶሐቦች ቁጥራቸው ትንሽ ቢሆንም በበድር ዘመቻ ላይ የጠላትን የተደራጀ ጦር አልፈሩም።